# የመስቀሉ ስር
# ቁማርተኞች

ከዲ/ን

በጋሻው ደሳለኝ

0911-46 41 22

የሽፋን ስዕል
ያሬድ እና ክብሮም

ታህሳስ 1998

አዲስ አበባ

## መግቢያ

መግቢያ የሌለውን ሰው መግቢያ
ጻፍ አትበሉት፡፡

# ክፍል 1

## አደጋ ጣዮች

«ከሞአብም አደጋ ጣዮች በየአመቱ ወደ ሀገሩ ይገቡ ነበር» ይላል፡፡
*የነገስታቱ መፅሐፍ 2ኛ ነገ 13፥20*

የምንኖርባት ፕላኔት አደገኞች የበዙባት፣ ዋይታና ጩኸት የማያጣት ልዩ የጦርነት ቀጠና ከሆነች ጊዜም እንደ ጅረት እየፈሰሰ አያሌ ዓመታት ተቆጠሩ - - -

ትናንት እንደቀልድ በወንድሙ አናት ላይ የድንጋይ በረዶ ያዘነበው ቃየንና ቃየናውያን የትላንትና ድንጋያቸውን በፕላስተር ቦንብ ለውጠው ዱላቸውን በአዳኝ ጥይት ቀይረው ዛሬ ዓለምን ከዳር ዳር ማንጫጫታቸው ምድር የአደገኞች መኖሪያ፣ የአሸባሪዎችም ዋሻ ብትሆን ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ሆኗል እንዳለው በእርግጥም እንደሆነው ከብዙ ዓመታት በፊት የባህር በር እየሰበሩ አሳቻ ጊዜን እየቆጠሩ ወደ ቅድስቲቱ ከተማ በመግባት አደጋን የሚጥሉና የሠላማዊውን ህዝብ ሠላም የሚያደፈርሱ ነውጠኞች ግልፅ በሆነ አማርኛ አደጋ ጣዮች ነበር የሚባሉት፡፡

ምሬት፣ ሞትና ጋኔን የተቆራኙት ህሊና ትኩስ ደም እንጅ የስሲሆም ፀበል ምኑም ባይደሰበት የእብደት ወረት ያሻውን ሲገድል ያሻውን ሲያጠፋ እንደጅብዱ ተቆጠረለት እንጅ ከዚህ ዓለም ውግዘት አልገጠመውም፡፡

በመጨረሻም በሳቱት ጊዜያውያን ላይ ብዕሬን እንዳነሳሁት ሁሉ ለቀናችዋ ሃይማኖት ክብር በእውነትና በፍቅር የሚደክሙትን ሊቃነጳጳሳቱን፣ ካህናቱን፣ ሰባክያነ ወንጌሉንና አሁን በዝማሬአቿው ምድርን እየከደኑ ያሉትን ዘማርያኑን ሁሉ ሳላመሰግን አላልፍም።

በተረፈ ግን ማንም አንዳች ቢጠይቀኝ የእኔ መልስ

«ዘጸሐፍኩ ጸሐፍኩ» የሚል ነው። ዮሐ. 19፥22

ይቆየን።